# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፤የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 10 ሐምሌ 17 2000 ዓ.ም


## ታጣቂዎች በተቀናጀ እቅድ አራት ሥፍራዎችን ተቆጣጠሩ፡፡

**"ሲለበለብ፣ እንኳን ሰው ወተትም ይገነፍላል"** የግንቦት7 አመራር

ሰኔ 29 2000 ዓ.ም ከእኩለ ሌሊት አንስቶ አስከ ሌሊቱ 10 ሰዓት ድረስ፣ የዓለም ከተማ፣ ታች ቤት ወረዳ ፌጠራ፣ መራኛና አሮሞ ዋጇ ቱሬ የተባሉ የሰሜን ሸዋ ስፍራዎች የመለስ ዜናዊን ግፈኛ አገዛዝ በሚቃወሙ ሃይሎች እጅ ወድቀው እንደነበር ተረጋገጠ።

ታጣቂዎቹ በአራቱም ስፍራዎች በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ሰአት በመግባት ስፍራውን ለመቆጣጠር እንደቻሉና በዚህም ጊዜ ባካባቢው ከነበሩ የፖሊስ ሃይሎችና ሚሊሻዎች ምንም ዓይነት ተቃውሞ እንዳልገጠማቸው የግንቦት 7 አስተማማኝ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡

ራሳቸውን "የአንድነት ሃይሎች" በማለት ለህዝብ ያስተዋወቁት እነዚሁ ታጣቂዎች፤ ሜጋፎን በመጠቀም ለአካባቢው ህዝብ ስለድርጅታቸው ዓላማ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡እንደ፡ግንቦት፡7 አስተማማኝ መረጃዎች፡ከሆነ፡ ታጣቂዎቹ ባደረጉት ቅስቀሳ፤ የሚንቀሳቀሱበት ዓለማ በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ላለማድረስ አልሞ የተነሳ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እስካሁን በአከባቢው የወያኔ ኢህአዴግ መሳሪያዎችና አገልጋዮች የነበሩ ግለሰቦችም ከእንግዲህ ወያኔ ኢህአዴግን በመተው እና ህዝቡንና የአንድነት ሃይሎችን በመቀላቀል የበደሉትን ህዝብ መካስ እንደሚገባቸው ያስገነቡት እነዚሁ ታጣቂዎች፤ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኞች እስከሆኑ ድረስ የአንድነት ሃይሎች አብረዋቸው ለመሥራት ፈቃደኞች እንደሆኑ አስረድተዋል። ታጣቂዎቹ፤ ከአራቱም ሥፍራዎች ከሌሊቱ 10 ሰዓት ለቀው ሲወጡ ወደ ሰማይ የሩምታ ተኩስ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን፤ በማግስቱ ጠዋት ታጣቂዎቹ የበተኗቸው በርካታ በራሪዎች በሁሉም ቦታዎች ተገኝተው በህዝቡ ተነበዋል።

ስለ ጉዳዩ የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራሮች በሰጡት አስተያየት "መለብልብ ሲበዛበት፤ እንኳን ሰው ወተትም ይገነፍላል" ብለዋል።

" ሰኔ 29 ቀን በሰሜን ሸዋ የታየው የታጣቂዎች እንቅስቃሴ የመለስ ዜናዊን ለከት ያጣ እብሪት ለማሰቆም በመላው ሃገሪቱ እያስገመገመ ከላው ቁጣ ካፈያው ነው የሚል እምነት አለን"ያሉት የግንቦት 7 መሪዎች፤"አፈናውና ግፉ ባፋጣኝ ሊቆም የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ካፈያው ወደ ጶፍነተ እንዳይቀየር የማድረግ ሀላፊነት ያለው፤ አሁንም ቢሆን በሥልጣን ላይ ባለው አገዛዝ ነው"ብለዋል።

"ይህ አይሆንም ብሎ በእብሪት ለመቀጠል ከፈለገ፣ ድርጊቱ ለሚያስከትለው መዘዝ ተጠያቂዎቹ ከአሁን በኋላ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ ብቻ ናቸው፡፡ በግንቦት 7 በኩል ግን፤ በሃገራችንና በዜጎቻችን ላይ የሚፈጸምን ግፍ ለማስቆም የኢትዮጵያ ህዝብ ከአሁን በኋላ በዜግነቱና በሰውነቱ ሊጎናጸፋቸው የሚገባውን መብቶች መለስን "ስጠኝ" ብሎ የሚለምንበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡ አስገድዶ ፈልቅቆ ይወስደዋል እንጂ" በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል-የንቅናቄው፡መሪዎች።

## የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራሮች ሐምሌ 13 2000 ዓ.ም በሎስ አንጀለስ ከተማ ታላቅ ስብሰባ አደረጉ

በሎስ አንጀለስ ከተማ በአሮማ ዊልሻየር ማዕከል እሁድ ሐምሌ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ8 ሰዓት ጀምሮ የንቅናቄውን ዓላማ ለመደገፍና ከንቅናቄው መሪዎች ጋር ለመወያየት ከመጡ ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት ለማድረግ ተችሏል። በሥፍራው ተገኝቶ የነበረው ሪፖርተራችን የስብሰባውን ዉሎ እንደሚከተለው ዘግቧል፡

በውይይቱ የንቅናቄው ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ "የህግ የበላይነት የሰለጠነ ፖለቲካ ትግል መሠረት ነው። አቶ መለስ ህግ በሆኑበት አገር ግን.." በሚል ርዕስ የንቅናቄውን ዓላማዎች፣ ለንቅናቄው መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች፣ የንቅናቄውን

ወደገጽ 2 ዞሯል

## የረሃብተኛው ቁጥር 10 ሚሊዮን ደረሰ (ቢቢሲ)

## አሁንም ህፃናት እንደቅጠል እየረገፉ ነው(ሬውተርስ)

በኢትዮጵያ የተለያዩ ስፍራዎች የተስፋፋው ረሀብ እጅግ እየከፋ በመጣበት በአሁኑ ወቅት፤ህፃናት በአስደንጋጭ ሁኔታ በምግብ እጦት እየሞቱ መሆናቸውን ሬውተርስ የዜና ወኪል ቪዲዮ አሰደግፎ ባሰራጨው ዘገባ አጋለጠ።በተለይ በደቡብ ክልል በሀዲያ ዞን በረሀብ ህፃናት ሲሞቱ፣ ወላጆችና ቤተሰቦች በረሀብ አንጀታቸው እየጮኹ ለልጆቻቸው መሪር ለቅሶ ሲያለቅሱና መሬት ቆፍረው ልጆቻቸውን ሲቀብሩ የሚያሳይ ዜና ያሰራጨው የሬውተርስ ዘጋቢ፤በአካባቢው የሚገኙ የጤና ባለሙያዎችን ዋቢ በማድረግም ብዙዎች በምግብ እጥረት መሞታቸውን፣በህይወት ያሉትም በአስጊ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸውን አመልክቷል።

የዜና ወኪሉ ይፋ ባደረገው ቪዲዮ በህይወት የተረፉ ናቸው ተብለው የታዩት ህፃናት፤ ሰውነታቸው እላያቸው ላይ የተጣበቀና አጥንታቸው የቀረ፣ሆዳቸው የተነፋ፣ጥርሳቸው ወደፊት የወጣ፣ጭንቅላታቸው በጣም የመሰለ፣ከዛሬ ነገ የሞት ተራቸውን የሚጠብቁ ናቸው።

ወደገጽ 2 ዞሯል

**"…አገራችንን ለመበታተን መሽቶ እስኪነጋ ትዕግስት ለሌላቸው ከህዲዎች ጊዜ ከሰጠናቸው፤ከጥቂት ዓመታት በሁዋላ የምናወራው ስለ ኢትዮጵያ ሳይሆን ስለሌላ፤ዛሬ ስሟን ስለማናውቃት አገር ይሆናል።የኢህአዴግ መንግስት ቀን ቆጥረን የምንጥለው መንግስት አይደለም።በተናጠል በሚደረግ ትግልም የሚገፋ አይደለም።ስለዚህ ዛሬ በአገራችን እየደረሰ ያለውን ድርብ ጥፋት ለማቆምና አገራችንን ለመታደግ የመጀመሪያው እርምጃ፤በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የምንል ሁሉ፤ወይም ዛሬ በመለስ ዜናዊ መርዘኛ ፖሊሲ የተለከፈው፤ኢትዮጵያዊ ወንድሜ፣እህቴ፣አባቴና እናቴ ናቸው የምንል ሁሉ፤ህዝባዊ መሰረት ያለው ጠንካራ ንቅናቄ መገንባት ይኖርብናል።"**

**አቶ ኤፍሬም ማዴቦ** የመጀመሪያውን ክፍል ገፅ 4 ይመልከቱ

# ርእሰ አንቀጽ

## ዜጎችና ሃገር ለተደፈቁበት ሁለንተናዊ ቀውስ፣ ፈውሱ ህዝብን የስልጣን ባለቤት ማድርግ ብቻ ነው፡፡

ህዝብ የስልጣን ባለቤት ይሁን ስንል፣ ህዝብ የስልጣን ባለቤት ከሆነ፣ ስልጣን ላይ ያወጣውን የማውረድ መብት ይጎናጸፋል ብለን ስለምናምን ነው ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ስልጣን ላይ የሚወጡ ግለሰቦች፣ የሞራልና የሃይማኖት ኮምፓስ ባይኖራቸው፣ ፈሪሃ አምላክ ባይዘራባቸው፣ ህሊናቸው ደንዝዞ ሁሉን ቁልቁል ቢያዩ፣ ስልጣን ላይ ያወጣቸውን ህዝብ ሊፈሩና ሊያከብሩ እንጂ ሊንቁ አይችሉም፡፡

ዋናው የመንግስት መፈጠር ምክንያት ሰውን በአውሬነት ከሚኖርበት ህገ-አራዊት አውጥቶ፤ የህግና የፍትህ ልእልና በሰፈነበት ማህበረሰብ እንዲኖር ማድረግ በመሆኑ የህዝብ የስልጣን የበላይነት በሰፈነበት ሀገር ባለስልጣናቱ ህግንና ፍትህን እንዳሻቸው እየረገጡ በስልጣን መቀጠል አይቻላቸውም፡፡

ህዝብ የስልጣን ባለቤት በሆነበት፣ ህዝብን በሚያዋርድ ድህነት ውስጥ የደፈቀ፣ በረሃብ እንዲረግፍ ምክንያት የሆነን የማይረባ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተይዞ በመመጻደቅ የስልጣን ባለቤት ተሁኖ የሚቀጠልበት ሁኔታም አይኖርም፡፡

ህዝብ በረሃብ እያለቀ ለጦር ሃይል በጀት መጨመር፣ ህዝብ በረሃብ እየረገፈ ጥቂቶች በልተው የሚያድሩበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ በሀገሪቱ የሚበላ ሳይጠፋ፣ እንኳን በመቶ ሺዎች ቀርቶ አንድ ህጻን በረሃብ የሚሞትበትን ሁኔታ ባላስልጣናቱ መፍቀድ አይቻላቸውም፡፡

ማንም ባለጊዜ እንዳሻው የሀገሪቱን መሬት ለማንም መሸጥ፣ ህዝቧን በሚያዋርድ የባእድ ሃገሮች እሽክርናና የዘለቄታ ጥቀሚን በሚጎዳ የውጭ ጣልቃ ገብነት ወንጀሎች መፈጸም ቀርቶ ለቅጽበትም ማሰብ አይችልም፡፡

ህዝብ የስልጣን ባለቤት በሆነበት ሃገር በቢሊዮኖች ቀርቶ በሽዎች የህዝብ ገንዘብ ዘርፎ 17 አመት ቀርቶ አንድ ቀን ማደር አይቻልም፡፡

የህዝብ መብት ገፎ፣ በአንድ ጀንበር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች ማሰርና በሺዎች የሚቆጠሩትን መግደል ቀርቶ የአንድ ንጹህ ዜጋ ጸጉር እንኳ መንካት አይቻልም፡፡

ህዝብ የስልጣን በላቤት በሆነበት ሃገር፣ የህዘብን አንድነት የሚያላላ፣ የዜጎች የደህንነትና የብልጽግና መሰረት የሆነውን የሃገራዊነት ስሜት የሚያወድሙ በርካታ ድርጊቶች መፈጸም ቀርቶ አንድም ጸረ ሃገራዊና ጸረ ህዝብ ቃል ባለስልጠናቱ መተንፈስ አይችሉም፡፡

ህዝብ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን ካስቻልን የመከራችን መጨረሻ የመጀመሪያውን እርምጃ ወሰደን ማለት ነው፡፡ ውሉን ወደ ማይስተው የብልጽግና፣ የደህንነት፣ የክብር፣ የነጻነት፣ የስልጡንነት፣ ሰብአዊነት ኢትዮጵያዊ እጣችን ወደ ሚሆንበት መንጎድ ጀመርን ማለት ነው፡፡ የቀወሶች ሁሉ መድህን፣ የችግሮች ሁሉ መፍትሔ፣ የማህበራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ በሽታዎች ሁሉ መድሃኒት ለሆነው ለህዝብ የስልጣን ባቤትነት መታገል ከፖለቲካ አጀንዳዎቻችን ሁሉ የላቀው አጀንዳችን መሆን አለበት ብሎ በየ ጊዜው ግንቦት7 የሚለፍፈው ለዚህ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን ጊዜ ለማፋጠን፣ በዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ፊት የተጋረጡትን ጋሬጣዎች ለመጥረግ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሁሉም ዜጎች ተባብረው ይቁሙ፤ የሁሉም ሃይል፣ የሁሉም እውቀት፣ የሁሉም ጉልበት ለዚህ አላማ ይፍሰስ እንላለን፡፡ የሁሉም የመደራጀት አለማ፣ የሁሉም የመታገያ አጀንዳ፣ የሁሉም የመታገያ ስልት ለእዚህ ግብ እስካልቆመ ድረስ ለሌላ የክህደት እና የአምባገነንነት አዙሪት በር ከፋች በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ስልጣን ከህዝብ ለሚመነጭበት ህልማችን መሰካት ዘብ ይቁም እንላለን!!

**በሎስ አንጀለስ ከተማ ታላቅ ስብሰባ** ከገጽ 1 የዞረ

የትግል ስልትና ያ ስልት የተመረጠበትን ምክንያት አንስተው ያብራሩ ሲሆን ሁሉንም በእኩልነት የሚያገለግሉ ተቋማት በሌሉበትና ግለሰቦች ህግ በሆኑበት ሀገር ህጋዊ ሰላማዊ ትግል ማድረግ እንደማይቻል አስረድተዋል።

ከአቶ አንዳርጋቸው በመቀጠል ንግግር ያደረጉት አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል አሁን በሃገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ምን እንደሚመስል አስረድተዋል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ወንጀል ነው እያለ ያለው የመለስ አገዛዝ እንደሆነ ሲያስረዱ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ያደረገው ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ወያኔ በጻፈው ህገ መንግስትም እውቅና የተሰጠው ሆኖ ሳለ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ እድሜ ልክ እንደተፈረደባቸውና በይቅርታም ሲፈቱ ቅንጅቱ ያቀረባቸውንና ብዙ ኢትዮጵያውያን የሞቱለትን አካለ ጎደሎ የሆኑበትን ከሥራና ከቀየ የተፈናቀሉበትን የነጻ ተቋማት ምስረታ ጥያቄዎች ደግመው ቢያነሱ ይቅርታው ተነስቶ መከሰስ ሳያስፈልጋቸው የእድሜ ልክ እስራት የሚጠብቃቸው መሆኑ ህጋዊ የሆነውን ሰላማዊ ትግል እንዳይቻል ማድረጉን ገልጸዋል። ስለሆነም የአቶ መለስ አገዛዝ ህጋዊ የሚለውን ትግል ለማድረግ ቢፈለግ እንኳ የዚያ ትግል ግብ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንደሚያዳግታቸው ገልጸዋል።

በስብሰባው ከተገኙት ሰዎች በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ማብራሪያ በንቅናቄው አመራሮች እንደተሰጠ ለማወቅ ተችላል። ይህ ዜና እየተጠናቀረ በነበረበት ወቅት በእንዲህ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እና አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል በላስ ቬጋስ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር የውይይትና የምክክር ስብሰባ በማድረግ ላይ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

**የረሃብተኛው ቁጥር 10 ሚሊዮን ደረሰ** ከገጽ 1 የዞረ

የዜና ወኪሉ ያናገራቸው የአካባቢው የጤና ባለሙያ ዶክተር አብርሐም አሸናፊ፤ የአካባቢው ህፃናት በሙሉ በምግብ እጥረት ሳቢያ በሚከሰተውና"ኩዋሽከር"በተባለው በሽታ እየተሰቃዩ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ወደ ህክምና ከሚመጡት መካከል 50 በመቶ ያህሉ እንደሚሞቱ ተናግረዋል።

እንደ አብርሐም አባባል የአካባቢው ነዋሪዎች በቀጣይ ጊዜያትም የሚያገኙት ሰብል ስለማይኖር ፤ችግሩ አሁን ካለበት ሁኔታም እየከፋ እንጅ እየተሻሻለ ይመጣል የሚል ተስፋም፣ግምትም የለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቢቢሲ ትናንት ባሰራጨው ዘገባ በኢትዮጵያ የረሃብተኛው ቁጥር ወደ 10 ሚልዮን ማሻቀቡን አስታውቋል።የተመድን መግለጫ ዋቢ በማድረግ የዜና አውታሩ እንደዘገበው ከአጠቃላዩ ህዝብ 12 በመቶ ለረሃብ የተጋለጠ ሲሆን በአስቸኳይ እርዳት ካልተደረገ ባጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ የከፋ እልቂት ሊከሰት እንደሚችል አስጠንቅቋል።በቅርብ አዲሱ ለገሰ፤የተከሰተው የምግብ እጥረት ችግር ከመንግስት ቁጥጥር አልወጣም፤አይወጣምም በማለት በወገን ላይ ማላገጡ አይዘነጋም።

**አዘጋጆች**
ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ
የቀድሞ የአዲስ ዜና እና የነጻነት ጋዜጣ አዘጋጆች

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፣አቶ ቸኮል ጌታሁን፣ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የነበሩ፡፡

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## አልቃይዳና የኢትዮጵያውያን ፈተና

በጽናት ፍቅሩ

አልቃይዳ ጓዙን ጠቅልሎ ከሜሶፖታሚያ(ኢራቅ) በመውጣት ላይ መሆኑን ገልፍ ኒውስ ሰሞኑን ዘግቧል። የአሜሪካ ባለስልጣናትም ዜናው እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል።የአልቃይዳ ኢራቅን ጥሎ መውጣት የአለምን ሰላም ለሚሹ ሀይሎች ሁሉ መልካም ዜና ቢሆንም ቡድኑ ኢራቅን ጥሎ የሚወጣው ሀይሉ በመዳከሙ ሳይሆን እራሱን ከአሜሪካ ጥቃት በመከላከል፣ለበለጠ ጥቃት የሚረዱትን ስትራቴጂክ ቦታዎች ለመምረጥ መሆኑን በዜናው ላይ ትኩረት እንድናደርግ ግድ ይለናል። በአልቃይዳ የተመረጡ እነዚህ ስትራቴጂክ ቦታዎች ደግሞ በሱዳንና በሶማሊያ የሚገኙ ናቸው። ቡድኑ በእነዚህ አገሮች ያለውን የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና የጸጥታ ችግሮች እንዲሁም በቅርቡ የታዩ ታሪካዊ ዳራዎችን ተጠቅሞ፣በአሜሪካ እና በጀሌዎቿ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ማቀዱ በአፍሪካ ቀንድ ለሚገኙ ዜጎች አስደንጋጭ ዜና ነው።። አሜሪካ እኤአ 1994 በሶማሊያ ውስጥ የደረሰባትን ችግር ካየች በሁዋላ ወደዚያች አገር እግረኛ ሰራዊቷን ላለመላክ እርም ብላለች።አልቃይዳም ይህን በደንብ ያውቃል።አሜሪካ ሶማሊያ ውስጥ ያለውን የቤት ስራ የምታሰራው በጀሌዋ ወያኔ በኩል መሆኑንም አልቃይዳ አብጠርጥሮ ያውቃል።ወያኔም በውስጥ ችግሩ ምክንያት፣በተለይ ሰራዊቱ “ለምን እርባና በሌለው ነገር እሞታለሁ” በማለት እየከዳው መሆኑንና በሶማሊያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ስራ ለመስራት የሚያስችል ሀቅም እንደሌለው ያውቃል። ስለዚህ እነዚህን ቦታዎች በመምረጡ፣በኢራቅ ከሚደርስበት ጥቃት እረፍት ያገኛል ብቻ ሳይሆን እራሱን እንደገና በማዋቀር በአሜሪካና በጀሌዎቿ ላይ ሰፊ ጥቃት ለመሰንዘር እንደሚችል ለመገመት ነቢይ መሆን አያስፈልግም ። ብዙ የአፍሪካ አገሮች በቡሽ መንግስት የቀረበውን የአሜሪካን ጦር በአፍሪካ የማስፈር እቅድ የተቃወሙት “አሜሪካ ባለበት አልቃይዳ አለ፣አልቃይዳ ባለበት አሜሪካ አለ” የሚለውን ምክር ግምት ውስጥ ስላስገቡ ነው። ሁለቱ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች፣ ኢትዮጵያና ጅቡቲ፣ ግን ይህን ምክር ወደ ጎን በመተው ለአሜሪካ ጦር በራቸውን ክፍት አድርገዋል። አልቃይዳም በተከፈተው በር ለመግባት ጓዙን ጠቅሎ እየመጣ ነው። እድሜ ለእነ መለስ ዜናዊ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ደህንነቶች መገደሉና በበሽታና በርሀብ መሞቱ ሳያንሰው ተጨማሪ የሞት ድግስ ከአረቦች ምድር ተጭኖ እየመጣለት ነው። ከእንግዲህ ተከታታይ የሰቆቃ ድምጾች የሚሰሙት፣በእየቴሌቪዥኑ ማቆችን ለብሰው የሚታዩት የኢራቅ እናቶች ሳይሆኑ የኢትዮጵያ እናቶች ይሆናሉ ማለት ነው፡፡የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ማነው?

ኢትዮጵያ በአፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ከሚገኙ የአረብ አገሮች ጋር ያላት የውጭ ግንኙነት በዋነኝነት በአራት ነገሮችን ላይ የተመሰረተ ነው።አንደኛው ከእስራኤልና ከፍልስጤም ጋር ተያይዞ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ የምትወስደው አቋም ነው።እስራኤል ከተመሰረተችበት ከ1948 ጀምሮ፣ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታትና በአፍሪካ ህብረት መድረኮች ላይ እስራኤልንና ፍልስጤምን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ስትወስዳቸው የነበሩት አቋሞች ገለልተኝነቷን የሚያመላክቱ ነበሩ።አንዳንድ ጊዜ ከእስራኤል ሌላ ጊዜ ከፍልስጤሞች ጎን በመቆም ከሁለቱም ወገኖች ደጋፊዎች ጋር ላለመላተም ስትሞክር ቆይታለች። ሁለተኛነገርየሀይማኖት ጉዳይ ነው።ኢትዮጵያን በተለምዶ የክርስቲያን አገር አድርጎ ማየቱ በአብዛኛው የአረብ አገሮች ዘንድ እየቀነሰ ቢመጣም፣ ስሜቱ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ብሎ መናገር አይቻልም። ነገር ግን አገሪቱ ሪፑብሊክ ከሆነችበት ጊዜ አንስቶ የተከተለችው ፖሊሲ፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በሀይማኖት ሰበብ ከሚነሳ ቀጥተኛ ግጭት ታድጓታል።

የውጭ ፖሊሲያችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሶስተኛው ነዳጅ ዘይት ነው።አብዛኛው የአገሪቱ ነዳጅ የሚገባው ከአረብ አገሮች በመሆኑ ከእነዚህ አገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት በነዳጅ አቅርቦቱ ላይ ተጽኖ አለው። በመጨረሻም የአባይን ወንዝ አለ።ይህም እንዲሁ ከግብጽ ሀያልነትና ተሰሚነት ጋር ተያይዞ የሚታይ ተጨማሪ ምክንያት ነው።ከላይ የተነሱት ነጥቦች ግምት ውስጥ ሲገቡ፣የአረቡ አለም ከተቀረው አለም ባላነሰ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም ላይ ተጽኖ ለማሳረፍ ትልቅ ሀይል አለው።የአረቡ አለም የራሱ የሆኑ ብዙ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም፣ከዚህ አለም ጋር የሚመሰረተው ግንኙነት በተቻለ መጠን በገለልተኝነት ላይ የተመሰረተ ቢሆን ይመረጣል።ወያኔ በአሁኑ ጊዜ እየተከተለ ያለው ፖሊሲ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን የህዝቦቿን ህልውናም አደጋም ውስጥ የሚጥል ነው። ለዚህ ማሳያው ደግሞ በሶማሌ ያደረገው ወረራና የአረቡ አለም ምላሽ ነው።ገና ለገና፣ “ተቃዋሚዎች በሶማሊያ የመደራጃ ቦታ ያገኛሉ፣ የአሜሪካ ዶላርም ይዘንባል፣በአሜሪካ ድጋፍም ለፈለግነው አመታት በስልጣን ላይ ለመቆየት እንችላለን” በሚል ስሜት ሶማሊያን መውረሩ፣ የወያኔን በስልጣን ላይ የመቆየት እድሜ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ህልውናም አደጋ ውስጥ እየከተተው ነው።ለእንጀራ ብለው ውትድርናን የተቀላቀሉ በርካታ ወጣቶች ለወያኔ እድሜ ማራዘሚያ ኪኒን በመሆን በሶማሊያ በረሀዎች እየረገፉ ነው። እንደቅጠል የሚረግፉት የመለስ ዜናዊ ወይም የባለስልጣኖቹ ልጆች ሳይሆኑ (የእነርሱ ልጆች ለአእምሮዋቸው ጤንነት ሲባል፣ጦርነትን በፊልም እንኳ እንዲያዩት አይፈቀድላቸውም) ለእንጀራ ብለው የተሰለፉት የድሀ ልጆች ናቸው።

ከሁለት አመታት በፊት፣ መለስ ዜናዊ በሶማሊያ ያለው ጦርነት በሁለት ሳምንታት ውስጥ ይጠናቀቃል ማለታቸውን ጠቅሰው የዘገቡ ጋዜጦች፣ ከሁለት አመት በሁዋላ የሚነግሩን የጦርነቱን ማለቅ ሳይሆን፣የአለቁ ወታደሮችን ቁጥር ነው።አሁን ደግሞ አልቃይዳ ወደ ሶማሊያና ወደ ሱዳን በመግባት የሚሞተውን ወጣት ቁጥር ለመጨመር ተዘጋጅቷል። የአልቃይዳ ጥቃት በባህሪው በወታደሮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን ሲቪሉን ህዝብም ኢላማ ያደረገ ነው። ይህ ማለት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰይወድ በግድ የጥቃት ኢላማ ይሆናል ማለት ነው።አልቃይዳ የኢትዮጵያ ህዝብ መለስ ዜናዊን ምን ያክል እንደሚጠላው አይገባውም።ለእነ መለስ የስልጣን እድሜና ሀብት ማከማቻ ተብሎ ወጣቱ በጦርነት እንደሚማገድም አይረዳም እናም ባገኘው ኢትዮጵያዊ ላይ ሁሉ ጥቃት ከመሰንዘር ወደ ሁዋላ አይልም።

የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ሰራዊቱ በወያኔ ላይ ተቃውሞ ማንሳት ይኖርበታል።እህቶቹ በአልቃይዳና በሌሎች ቡድኖች የጥቃት ኢላማ ይሆናሉ። ሰራዊቱ መሞቴ ይብቃ ብሎ ከወያኔ ጋር ግብግብ መግጠም አለበት።የራሴን ነፍስ ብቻ ሳይሆን የአገሬን ህልውናም አድኜ ለተተኪው ትውልድ ማሸጋገር አለብኝ ብሎ ማሰብ አለበት። ለአገርና ለህዝብ መኖር ማለትም ይህ ነው።ይህን ካላደረገ እየኖረና እየሞተ ያለው ለእነመለስ ዜናዊ ነው ማለት ነው። ለግለሰቦች መሞትና ለህዝብ መሞት ደግሞ በጣም የተለያዩ ናቸው።

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## “በፍፁም የማይለወጠው፤ የቆምንለት ዓላማና ፅኑ የሆነው የማሸነፍ እምነታችን ነው”

### አቶ ኤፍሬም ማዴቦ

*ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለዲሞክራሲና ለነፃነት ንቅናቄ ፤ባለፈው እሁድ በዋሽንግተን ዲሲ በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ከንቅናቄው አባላት አንዱ የሆኑት አቶ ኤፍሬም ማዴቦ የተሳታፊዎቹን ቀልብ ሰቅዞ የያዘ ንግግር አቅርበዋል።ከአምዳችን ውሱንነት አኳያ ንግግራቸውን በአንድ ጊዜ ማቅረብ ባንችልም፤ በሁለት ተከታታይ ክፍል ለማቅረብ ወስነናል። ክፍል አንድ እነሆ፦*

ባለፉት አምስት አመታት ስለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ብዙ ተብሏል። በእጥፍ አደገ፤ ታይቶ በማይታወቅ እድገት አደገ፤መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጋር ልንቀላቀል ነው ሌላም…

የሀገሪቱ ጂ.ዲ.ፒ ከ2000 ጀምሮ እያደገ ነው ቢባልም፤የህዝባችን የኑሮ ደረጃ የዛሬ 45 ዓመት ከነበረው ፈቀቅ አላለም። በ 2006 የኢትዮጵያ ጂ.ዲ.ፒ 19.1 ቢሊዮን ዶላር እንደነበር ሲነገር፤ በዚሁ ዓመት 44 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን ከድህነት መስመር በታች ነበር የሚኖረው። የተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚ መለኪያና ሌሎችም ተዛማጅ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ በችግርና በድህነት ከታች ወደ ላይ 3 ኛዋ አገር ናት።

በፖለቲካው መስክ

- በምስራቅ የማያስፈልግ የውክልና ጦርነት ውስጥ ተዘፍቀናል በሰሜን ደግሞ ወደማያስፈልግ ጦርነት እያዘገምን ነው።
- በ2005 በድንግዝግዙም ቢሆን ታይቶ የነበረው የፓለቲካው ብልጭታ ዛሬ ደብዛው ጠፍቶ የህ.ወ.ሀ.ት አመፀኞች የፓለቲካና የ ኢኮኖሚ ጡንቻቸውን እያዳበሩ ይገኛሉ።
- ዛሬ ኢትዮጵያውያን የነፃነትና የመብት ተሟጋቾችን ለማየት የፈለገ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ሰው ቃሊቲ መሄድ አለበት።
- የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ለ አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተፈቷል ተብሎ ቢፏለልም፤ዛሬ ኢትዮጵያን ያንገሸገሻት ለቁጥር የሚታክተው የነፃ አውጭ ድርጅት ብዛት ነው።
- ረሀብ -ረሀብን በተመለከተ ስለ አገራችን ብዙ ተብሏል።የ አገሪቱ ኢኮኖሚ አድጓል ቢባልም፣ትርፍ የ እርሻ ምርት ተመረተ ቢባልም፤የ አገራችን ህዝብ እንደገና ተረቧል።ለምን አይራብ?አገራችን ላይ በሁሉም መስክ የሚደረገውን ነገር ሁሉ የሚወጥኑት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው።
- አንድነት _የአገራችን ድንበር እንደሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች”እዚህ ነው፤እዚያ ነው” እየተባለ በቀኝ ገዥዎች በትር የተሰመረ፣የተካለለ አይደለም።ይልቁንም አገራችን ቅኝ ገዥዎች የራሳቸውን ድኢንበር በውል ከማወቃቸው በፊት የተካለለ ድንበር የነበራት አገር ናት።

የዛሬው የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የ ኢትዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት ናቸው ይላል።መንግስት ሉዓላዊነት የማስጠበቅ ሀላፊነት ቢኖረውም፤የሉዓላዊነት ባለቤትም፤ባለአደራም ህዝብ ነው።

ወገኖቼ! በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ኢትዮጵያ ላይ ባለን መለስተኛ ፍላጎቶች ዙሪያ መደራደር እንችላለን።ነገር ግን የሁላችንም ኢትዮጵያዊነት ቫሊዩ{እሴት} አንድ ነውና በኢትዮጵያ በራሷ፣በ አፈሯ፣በህዝቦቿና በድንበሯ ምንም ዓይነት ድርድር የለም።{ጭብጨባ አስተጋባ….}

እንግዲህ ይህን ሁሉ ካልንና ከተነጋገርን ዋናው ቁም ነገር “ምን ማድረግ አለብን?” የሚለው ጥያቄ ነው።-ምን ማድረግ አለብን? ? {አዳራሹ በፀጥታ ድባብ ተዋጠ።}

አቶ ኤፍሬም ቀጠሉ፦“…ዛሬ የ አገራችን ኢኮኖሚና ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ፤ያ የምንኮራበት የግዛት አንድነታችንም ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቋል። አገራችንን ለመበታተን፤መሽቶ እስኪነጋ ትዕግስት ለሌላቸው ከሀዲዎች ጊዜ ከሰጠናቸው፤ከጥቂት ዓመታት በሁዋላ የምናወራው፤ስለ ኢትዮጵያ ሳይሆን ስለሌላ፤ዛሬ ስሟን ስለማናውቃት አገር ይሆናል።የኢህአዴግ መንግስት ቀን ቀጥረን የምንጥለው መንግስት አይደለም።በተናጠል በሚደረግ ትግልም የሚገፋ መንግስት አይደለም።ስለዚህ ዛሬ በአገራችን እየደረሰ ያለውን ድርብ ጥፋት ለማቆምና አገራችንን ለመታደግ የመጀመሪያው እርምጃ””በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል” የምንል ሁሉ፤ወይም ዛሬ “በመለስ ዜናዊ መርዘኛ ፖሊሲ የተለከፉት ኢትዮጵያዊ ወንድሜ፣እህቴ፣አባቴና እናቴ ናቸው”የምንል ሁሉ፤ህዝባዊ መሰረት ያለው ጠንካራ የፖለቲካ ንቅናቄ መፍጠር ይኖርብናል።{ጭብጨባ አስተጋባ}

ሁለተኛውና የመጨረሻው ክፍል ሳምንት ይቀርባል።